www.chilot.me


| 3ኛ ዓመት ቁጥር 2<br>3rd Year No 2 | ሐረር ነሐሴ 17/1990<br>Harar August 23/1998 |
|---|---|

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ
# HARAR NEGARI GAZETA
## HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

| ያንዱ ዋጋ 1:00 | በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272 |
|---|---|---|



**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር 8/1991
የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 3/1988ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ። ------------------ ገጽ 39


## አዋጅ ቁጥር 8/1991 ዓ.ም
## የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 3/1988ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 3/1988ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

1. *አጭር ርዕስ*

ይህ አዋጅ የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 3/1988ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 8/1991 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. *ማሻሻያ*

የክልሉ ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 3/1988 እንደ ሚከተለው ተሻሽ ሏል።

1. አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 2 ተሠርዟል።
2. አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 1 ተሽሮ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 1 ተተክቷል።

« 1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 29 እና 30 የተደነገጉት ሁኔታዎች እንደ ተጠበቁ ሆነው የክልሉ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በሙስሊሙ ህብረተሰብ

www.chilot.me



መካከል የሚነሱና በተከራካሪዎች ፈቃድ ቀጥሎ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ የመዳኘት ስልጣን ይኖረዋል።»

3. በአንቀጽ 37 ስር ከንዑስ አንቀጽ 3 ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ 4 እንደሚከተለው ተጨምሯል።

« 4. የዳኞችንና የሬጂስትራሮችን ደመወዝ፣ ደረጃ፣ እርከን፣ ዝውውር፣ አበል፣ ህክምና፣ እድገትና የመሳሰሉት ጉዳዮችን ወስና ለምክር ቤቱ ጽ/ቤት በማቅረብ ሲጸድቅም በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል አፈጻጸሙንም ይከታተላል።»

4. አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 2 እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

« 2. ጉባኤው ቀጥሎ የተመለከቱትን አባላት ይኖሩታል።

(ሐ) በሕዝብ ተወካዮች ጉባኤ 2 አባላት በአባልነት

(መ) ከሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ 2 አባላት በአባልነት

5. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ማሻሻያ አዋጅ ከነሐሴ 17 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ሐረር መስከረም 25 ቀን 1991 ዓ.ም

አብዱላሂ ኢድሪስ

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ

መንግሥት ፕሬዝዳንት